# የተማሪዎች እገዳ/መባረር ደንቦች

የአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤት ቦርድ በተቻለ መንገድ ከእገዳ ይልቅ ሌላ አማራጭ የሥነ ሥርዓት እርምጃ ያበረታታል። እና ወደ መባረር ሊያደርስ የሚችል ባህሪ ለማሻሻል አስፈላጊ ድጋፍ ይሰጣል። ኤሲፒኤስ ባለብዙ ደረጃ የድጋፎች ሥርዓት(MTSS) የመልሶ ማቆቆም(ሪስቶራቲቪ ፕራክቲስ) ጭምር የያዘ የጥሩ ባህሪ ጣልቃ ገብነት አሰራር ይጠቀማል። ነገር ግን የተማሪዎችንና የሰራተኞችን ደህንነት ለማስጠበቅ ሲባል አንዳንድ ጊዜ የደንብ መተላላፉ መጠን የከፋ ሲሆን እገዳን ወይም መባረርን ሊያስከትል ይችላል። ስለ ባለብዙ ደረጃ የድጋፎች ሥርዓት(MTSS) በየደረጃ ሊወሰዱ ስለሚችሉ እርምጃዋች ዓይነት ተጨማሪ መረጃዋች በተማሪዎች ባህሪ ደንብ ላይ ይገኛል።

## I. ትርጓሜዎች

በJGD/JGE ፖሊሲና በዚህ ደንብ አገልግሎት ላይ እንደዋለው፤

**“አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም”** በእነዚህ ብቻ ባይገደብም የሚከተሉትን ያካትታል፤ የማታ ትምህርት፣ የአዋቂዋች ትምህርት፣ መደበኛው የትምህርት ፕሮግራም ለእነሱ አግባብነት የሌለው መሆኑ ሲገመት ሌላ በተለይ የተዘጋጀ የትምህርት ፕሮግራም ።

**“አፍራሺ ጉጂ ወይም ፈንጂ መሣሪያ”** ማለት (1) ማንኛውም ፈንጂ፣ ተኳሽ ወይም የመርዝ ጋዝ፣ ቦንብ፣ የእጅ ቦንብ፣ ሮኬት ከሦስት አውንስ በላይ በመለኮሻ መተኳሻ ያለው ተቀጣጠይ ወይም ተመሳሳይ መሣሪያ፤(2) ማንኛውም መሳሪያ የማደኛ ጠበንጃ ወይም የማደኛ ጠበንጃ ቀለህ በአጠቃላይ ለአደን ስፖርት በተለይ እንደሚውል የሚታመንበት ካልሆነ በስተቀር በማንኛውም ስም የሚታወቅ በቀላሉ በሚቀጣጠል ፈንጂ የሚወረወር ወይም ሌላ ኋይል እና የመተኮሻ ቀዳዳ ከግማሽ ኢንች በላይ ስፋት መጠን ያለው እና (3) በማንኛውም መንገድ የተሰራ ወይም ማንኛውንም መሳሪያ ወደ ጎጂ መሳሪያ የሚቀየር ወይም ጎጂ መሳሪያ በቀላሉ መገጣጠም የሚችል ማለት ነው። አፍራሺ ጎጂ መሣሪያ ማንኛውንም መሳሪያ እንደ ጠበንጃ መሳሪያ ዲዛይን ያልተደረገ ወይም እንደገና ዲዛይን ያልተደረገ መሳሪያን ማካተት አይኖርበትም ወይም ማንኛውንም በቅድሚያ እንደ ጦር መሳሪያ የተዘጋጀ እና እንደገና ለምልክት መስጫ፣የችቦ ማብሪያ (ፖይሮቴኒክ)፣ መስመር ማሳያ ገመድ መተኮሻ፣ ለደህንነት ማስጠበቂያ ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት እንደገና የተሰራን አይጨምርም።

**“የሚበጠብጥ ተግባር/ባህሪ”** ማለት ማንኛውንም ተግባር የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ሥራዋች እና ሂደቶች እንዲቆረጥ የሚያደርግ ወይም ለተማሪዋች እና ለሌሎችም ጤንነትና ደህንነትና አደጋ የሚያስከትል ወይም የሚረብሽ ወይም የማስተማር ሂደቱን የሚያደናቅፍ ነው።

**“ማግለል”** ማለት አንድ የተባረረ ወይም ከሰላሳ ቀናት በላይ ለረዥም ጊዜ ትምህርት እንዳይከታተል በሌላ የትምህርት ቤት ቦርድ ወይም በግል ትምህርት ቤት በቨርጂኒያ ውስጥ ወይም በሌላ ስቴት የተከለከለን ተማሪ በትምህርት ቤት ቦርድ እንዳይገባ መከልከል ነው።

**“መባረር”** ማለት በትምህርት ቤት ቦርዱ በሚወሰን የሥነ ሥርዓት እርምጃ አንድ ተማሪ በትምህርት ቤት ክልሉ(ዲቪዝኑ) ውስጥ ባሉ ትምህርት ቤቶች ትምህርት እንዳይከታተል ማገድ እና የማባረር ውሳኔ ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ባሉት 365 ቀናት ተመልሶ ወደ ትምህርት ለመግባት እጪ ያልሆነ ነው።

**“የጦር መሣሪያ”** ማለት በቨርጂኒያ ሕግ § 18.2-308.1 መሰረት በትምህርት ቤት ንብረት ወይም ትምህርት ቤቱ ኋላፊነት በሚካሄድ የእንቅስቃሴ ሥፍራ የተከለከለ ማንኛውም መሳሪያ ወይም (1) ማንኛውም መሳሪያ የስፖርት ውድድር ማስጀመሪያ ሽጉጥ፣ ኑዮማቲክ ሽጉጥ (ቀለም የሚተፊ፣ቢቢ(BB) ወይም አየር የሚረጭ ጠበንጃ) ጭምር አንድ ነጠላ ወይም በተከታተይ ተወርዋሪ ነገሮችን ማፈናጠር የሚችል ተቀጣጣይነት ያላቸው ንጥረ ነገሮች በማፈንዳት ወይም በአየር ግፊት ሃይል በኒዮማቲክ ግፊት በመፍጠር ፤ (2) የዚህ ማቀፊያ ወይም የዚህ ዓይነት መሳሪያ መቀበያ፣ (3) ማንኛውም የጠበንጃ ድምፅ ማፈኛ ወይም የድምፅ መቀነሻ ፤ (4) ማንኛውም አጥፊ ጎጂ መሳሪያ ወይም (5) ማንኛውም ጥይት ያልጎረሰ በተዘጋ መያዣ ውስጥ ያለ የጦር መሳሪያ ነው።

**"የረዥም ጊዜ እገዳ"** ማለት ማንኛውም የዲስፒሊን የሥነ ሥርዓት እርምጃ ሲሆን ተማሪው ከ11-45 የትምህርት ቀናት ትምህርት እንዳይከታተል የሚታገድበት ነው። የረዥም ጊዜ እገዳ ከ45 የትምህርት ቀናት እገዳ ሊበልጥ ይችላል ነገር ግን ከ364 ቀናት መብለጥ የለበትም (i.) ጥፋቱ በቨርጂኒያ ሕግ §§ 22.1-277.07 ወይም 22.1-277.08 በተዘረዘረው መሰረት ወይም የከፋ የአካል ጉዳት የደረሰ ከሆነ ወይም (ii.) በቨርጂኒያ የትምህርት ዲፓርትሜንት አተረጓጎም መሰረት የትምህርት ቤት ቦርዱ ወይም ሱፐር ኢንቴንዳንቱ(ዋና ሥራ አስኪያጁ) ወይም በተወካዮ የሚያባብስ ሁኔታዎች መኖራቸውን ከተረዱ ።

**"አንድ ዓመት"** ማለት በፌደራል ደንብ የጊዜ መቁጠሪያ 365 ቀናት ነው።

**"የትምህርት ቤት ንብረት"** ማለት ማንኛውም የሕንፃ ወይም የማይቀሳቀስ ቋሚ ንብረት በትምህርት ቤቱ ወይም በቦርዱ ባለቤትነት ወይም በተከራይነት የተመዘገበና በትምህርት ቤት ቦርዱ ወይም በት/ቤት ቦርዱ ስም በስራ የዋለ ማለት ነው።

**"የአጭር ጊዜ እገዳ"** ማለት ማንኛውም የዲሲፕሊን ሥነ ሥርዓት እርምጃ ሲሆን ተማሪው ከ10 ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ትምህርት እንዳይከታተል የተከለለ ነው።

**"የሱፐር ኢንቴንዳንቱ(ዋና ሥራ አስኪያጁ) ተወካይ"** ማለት የሰለጠነ አቤቱታ የሚሰማ ወይም ባለሙያ ሰራተኛ በትምህርት ቤት አስተዳዳር(ዲቪዥኑ) የአስተዳደር ቢሮ ውስጥ ያለ በቀጥታ ለሱፐርኢንቴደንቱ (ዋና ሥራ አስኪያጁ) ወይም ለተወካዮ ተጠሪ የሆነ እና በትምህርት ቤት ውስጥ በሚገኝ የአስተዳደር ወይም ትምህርት አሰጣጥ ስራ ቀጥታ ተሳታፊ ያልሆነ ሰራተኛ ነው ።

## II. ለእገዳ ወይም ለመባረር የሚያደርሱ ሁኔታዎች

A. በተማሪዎች የባህሪ ደንቦች እና በትምህርት ቤት ቦርድ ፖሊሲዎች የተቀመጡት የጥፋት ምሳሌዎች **ለእገዳ የሚያደርሱ ሁኔታዎች** የሚከተሉትን ይጨምራል ነገር ግን በእነዚህ ብቻ አይወሰንም፤

- እሳት ሆን ብሎ ማስነሳት
- መዛት ወይም ማስፈራራት
- ድብድብ ጥቃት/ፀብ
- ስራ እንዳይካሄድ የማወክ ተግባር/ባህሪ
- አፀያፊ ወይም ነውር ቋንቋ
- ቁማር
- አልኮል ወይም ሌላ እፅ ወይም የተከለከለ ንጥረ ነገር መጠቀም፣ መያዝ ወይም ማከፋፈል
- ንብረት ማበላሸት
- የትምህርት ቤት ኃላፊዎችን ትእዛዝ አለመቀበል
- መሳሪያ መያዝ
- ስርቆት
- የትምህርት ቤት አውቶብስ ደንቦችን መተላለፍ
- ያለ ፍቃድ በአንድ ቦታ መገኘት
- የቡድን ወንጀል ስራ
- ሲጋራ መያዝ ወይም መጠቀም
- የወሲብ ጥቃት
- የወሲብ ማዋከብ ማስቸገር

ማንኛውንም ተማሪ ድርጊት የሚመለከት ከአካባቢው የህግ አስከባሪ አካላት ለዋና ሥራ አስኪያጁ(ሱፐርኢንቴደንቱ)

ሪፖርት የደረሰው ጉዳይ በትልቅ ሰው ቢፈጸም እንደ ፌሎኒ ወንጀል የሚታይ ከሆነ ወይም በህጉ መሰረት በVIII.B. ከታች በተገለፀው መሰረት ሪፖርት መደረግ ካለበት።

B. በተማሪዎች የባህሪ ደንቦች እና በትምህርት ቤት ቦርድ ፖሊሲዎች የተቀመጡት የጥፋት ምሳሌዎች **ለመባረር የሚያደርሱ ሁኔታዎች** የሚከተሉትን ይጨምራል ነገር ግን በእነዚህ ብቻ አይወሰንም፤

- እሳት ሆን ብሎ ማስነሳት
- መዛት ወይም ማስፈራራት
- ድብድብ ጥቃት/ፀብ
- ቁማር
- አልኮል ወይም ሌላ እፅ ወይም የተከለከለ ንጥረ ነገር መጠቀም፣ መያዝ ወይም ማከፋፈል
- የትምህርት ቤት ኋላፊዎችን ትእዛዝ አለመቀበል
- መሳሪያ መያዝ
- ስርቆት
- የትምህርት ቤት አውቶብስ ደንቦችን መተላለፍ
- የቡድን ወንጀል ስራ
- የወሲብ ጥቃት
- የወሲብ ማዋከብ ማስቸገር
- በአካባቢው የህግ አስከባሪ አባላት ለሱፐር ኢንቴንደንቱ (ለዋና ሥራ አስኪያጁ ) ወይም ለተወካዮ የሚደረጉ ሪፖርቶች በአዋቂ ቢፈፀም ወንጀል ሊሆን የሚችል ጥፋት አንድ ወጣት ፈፀሞል የሚውል ማስታወሻ ሲደርሰው ወይም በVIII.B. መሰረት በሕግ ሪፖርት መደረግ እንዳለበት ከተደነገገ

## III. ለእገዳ ወይም ለመባረር አቤቱታ ማቅረብ

A.የአጭር ጊዜ እገዳ

ለአስር (10) ቀናት ወይም ከዚያ ላነሰ ጊዜ እገዳ የሚመለከት አቤቱታ የማቅረብ አሰራር በ JGD/JGE ፖሊሲ በዝርዝር ተገልፃል። አቤቱታውን በሚመለከት የዋና ሥራ አስኪያጅ(ሱፐር ኢንቴንደንት) ውሳኔ የመጨረሻው ሲሆን ከዚያ አልፎ አቤቱታ ለትምህርት ቤቱ ቦርድ ማቅረብ አይችልም።

B. የረዝም ጊዜ እገዳ

ከአስር ቀናት በላይ ለሚቆይ እገዳ ተማሪው እና የእርሱ/የእርሷ ወላጅ(ዎች)/አሳዳጊ(ዎች) የዋና ሥራ አስኪያጅ(ሱፐር ኢንቴንደንት) ወይም በተወካዩ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የዋና ሥራ አስኪያጅ(ሱፐር ኢንቴንደንት) ወይም የተወካዩን ውሳኔ ባገኙ አምስት(5) ቀናት ውስጥ ለትምህርት ቤት ሙሉ ቦርድ ማቅረብ ይችላሉ። የትምህርት ቤት ቦርዱ የይግባኝ ጥያቄው በቀረበ በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት። የዚህ ይግባኝ አቀራረብ እና የሚቀርብበት ጊዜ በተመለከተ በJGD/JGE ፖሊሲ በዝርዝር ተገልፃል።

C. ማባረር፤

ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ሊባረሩ ይችላሉ የታሰበውን እርምጃ እና ምክንያቱን እና አቤቱታ ለትምህርት ቤት ቦርዱ የማቅረብ መብቱን የሚገልፅ የፅሁፍ ደብዳቤ ለተማሪው እና ለወላጅ/አሳዳጊ ከተሰጠ በኋላ። የማባረሪያ ደብዳቤው በደረሰው አምስት(5) ቀናት ውስጥ ይግባኝ ለሙሉ የትምህርት ቤቱ ቦርድ ማቅረብ ይቻላል። ለትምህርት ቤት ቦርዱ የቀረበው ይግባኝ ላይ በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መሰጠት አለበት። የዚህ ይግባኝ አቀራረብ እና የሚቀርብበት ጊዜ በተመለከተ በJGD/JGE ፖሊሲ በዝርዝር ተገልፃል።

ተማሪው ያለውን ይግባኝ የማቅረብ መብት ተጠቀመበትም አልተጠቀመበትም የትምህርት ቤቱ ቦርዱ የቀረበውን የማባረር ሃሳብ ማፅደቅ ወይም እንዲነሳ ማድረግ ይኖርበታል።

## IV. የተባረረ ተማሪዋችን ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ አሰራር

በፖሊሲ JGD/JGE እንደተገለፀው የሱፐር ኢንቴንደንቱ የሚከተለውን የአሰራር እና የጊዜ ቅደም ተከተል ያዘጋጀ ሲሆን ይህንኑ በመከተል የተባረሩ ተማሪዋች አቤቱታ ማቅረብ እና ተመልሶ ወደትምህርት ቤት ለመግባት ማመልከት ይችላሉ።

ከአሌክሳንደሪያ ከተማ የህዝብ ትምህርት ቤቶች የተባረሩ ተማሪዋች እና በተባረሩበት ወቅት ወደ መደበኛው ትምህርት ለመመለስ ፈቃድ ያልተሰጣቸው ከሆነ ወይም በአማራጭ የትምህርት ፕሮግራም ተመልሶ ለመግባት ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ ከተባረረበት ቀን አንድ(1) ዓመት በኋላ ። ማንኛውም የተባረረ ተማሪን መልሶ ለማስገባት ያለው አሰራር እንደሚከተለው ነው፤

A. ተማሪው በወቅቱ ተመልሶ ለመግባት እድል ማግኘቱን ለማረጋገጥ የትምህርት ቤት ቦርዱ ተማሪው እንዲባረር ውሳኔውን የሰጠበትን ደብዳቤ ከተፃፈበት ቀን ከዘጠኛ(9) ወራት አስቀድሞ እና ከአስር(10) ወራት በኋላ ተመልሶ ለመግባት ማመልከቻ መቅረብ አይኖርበትም። ተመልሶ ለመግባት በወቅቱ ማመልከቻውን ማቅረብ አለመቻል በማመልከቻው ላይ የሚሰጠውን ውሳኔ ለማዘግየት ምክንያት ሊሆን ይችላል። ማመልከቻው በፅሁፍ መቅረብ ያለበት ለኤሲፒኤስ የተማሪዋች አገልግሎቶች፣ አማራጭ ፕሮግራሞች እና ፍትሐዊነት ዲፖርትሜንት ነው። እድሜው ከአስራ ስምንት (18) እና ከዚያ በላይ የሆነ ተማሪ ማመልከቻውን የሚያዘጋጀው በራሱ ስም መሆን አለበት። ተማሪው እድሜው ከአስራ ስምንት ዓመት በታች ከሆነ ወላጁ ወይም አሳዳጊው በተማሪው ስም ማከናውን ይችላል።

B. እንደገና መልሶ ለመግባት ማመልከቻ በቀረበ በሃያ አንድ (21) ቀናት ውስጥ የተማሪዋች አገልግሎቶች፣ አማራጭ ፕሮግራሞች እና ፍትሐዊነት ዲፖርትሜንት የቀረበለትን አቤቱታ ለመመልከት ቀነቀጠሮ ለተማሪዋች አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈፀሚ ይይዛል። አቤቱታው በሚታይበት ወቅት ተማሪው እና/ወይም ወላጅ(ጆች) / አሳዳጊዋች ልጁ ተመልሶ እንዲገባ ለምን እንደሚፈልጉ፣ እንዴት ትምህርት ቤቱ የልጁ ተማሪ ባህሪ የተሻሻለ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚችል እና የዚህ ዓይነቱ ተገቢ ያልሆነ ባህሪ በድጋሚ እንደማይከሰት መልስ አዘጋጅተው ለማስረዳት መመጣት አለባቸው ። ልጁ በሚባረርበት ወቅት በትምህርት ቤት ቦርዱ ልጁ ለመመለስ ማሟላት አለባቸው ብሎ ያስቀመጣቸው ሁኔታዋች ካሉ የአቤቱታ መመልከት ሂደቱ እነዚያ ሁኔታዋች የተሟሉ ስለመሆናቸው ይመለከታል። የተማሪዋች አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈፀሚ ወይም ተወካዮ አቤቱታውን ባዳመጠ በሰባት (7) ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በፅሁፍ ያሳውቃል። ወላጅ(ዋች) /አሳዳጊ(ዋች) እና/ወይም ተማሪው የውሳኔው ኮፒ ይደርሳቸዋል።

C. ወላጅ(ዋች)/አሳዳጊ(ዋች) እና/ወይም ተማሪው የተማሪዋች አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈፀሚ ወይም ተወካዮ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለ ውሳኔው በደረሰው በአምስት ቀናት ውስጥ ለትምህርት ቤት ቦርድ ማቅረብ ይችላል። በተማሪዋች አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈፀሚ ወይም ተወካዮ የተሰጠው ውሳኔ ኮፒ፣ የመባረር ውሳኔ የተላለፈበት ኮፒ፣ እና ከመባረሩ ጋር በተያያዘ ተዛማጅነት ያላቸው የቀረቡ ሰነዶች ኮፒ፣ እና ተመልሶ ለመግባት የቀረበው ማመልከቻ ኮፒ ለቦርዱ ይቀርባል። ቦርዱ ካስፈለገው አቤቱታ የማዳመጥ ሌላ ፕሮግራም ሊያካሂድ ይችላል። ቦርዱ አቤቱታ ከተመለከተ በኋላ ባለው ሃያ አንድ (21) ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ያሳውቃል።

D. ተመልሶ ለመግባት የቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ካጣ ተማሪው (ወይም የሚመለከተው ከሆነ የእርሱ/እርሷ ወላጅ(ዋች) / አሳዳጊ(ዋች) እንደገና በዓመቱ ማመልከት እላይ በተጠቀሰው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ማቅረብ ይችላሉ።

## IV. *የአካል ጉዳት ያለውን ተማሪ ሥነ ሥርዓት እርምጃ አወሳሰድ*

በተማሪዎች ባህሪ ደንብ እና በ JGDA ፖሊሲ እንደተገለፀው ኤሲፒኤስ ከአካል ጉዳት ካላቸው ሰዎች የትምህርት አዋጅ (IDEA) እና የ 1973 የመልሶ ማቋቋም አዋጅ ክፍል 504 ደንብ ተከትሎ የሥነ ሥረዓት አሰጣጡ የሚከናወን ይሆናል

የፀደቀው፤ ሴፕቴምበር 5፣ 1996
የተሻሻለው፤ ጁላይ 10፣ 1997
የተሻሻለው፤ ጁን 18፣ 1998
የተሻሻለው፤ ጁላይ 12፣ 2001
የተሻሻለው፤ ጁላይ 1፣ 2005
የተሻሻለው፤ ጁን 15፣ 2006
የተሻሻለው፤ ዲሴምበር 19፣ 2013
የተሻሻለው፤ ዲሴምበር 18፣ 2014
የተሻሻለው፤ ጁን 11፣ 2015
የተሻሻለው፤ አክቶበር 25፣ 2018

የሕግ ማጣቅሻ፤ 20 U.S.C. § 7151.

የቨርጂኒያ ሕግ፣ 1950፣ እንደተሻሻሉት አንቀፃች §§ 15.2-915.4, 16.1-260, 18.2-119,18.2-308.1, 18.2-308.7, 18.2-308.8.2:2, 22.1-200.1, 22.1-254, 22.1-276.01, 22.1-276.2, 22.1-277, 22.1-277.04, 22.1-277.05, 22.1-277.06, 22.1-277.07, 22.1-277.07:1, 22.1-277.08, 22.1-277.2, 22.1-277.2:1, 22.1-279.3:1.

(8) -560-10

የቃላት መፍቻ፤

| | |
|---|---|
| GBEB | በትምህርት ቤት የሰራተኛ መሳሪያ |
| IGBH | አማራጭ የትምህርት ፕሮግራሞች |
| JEC | የትምህርት ቤት ምዝገባ |
| JFC | የተማሪ ባህሪ |
| JFC-R | የተማሪ ባህሪ መመዘኛ ደረጃ |
| JFCD | በትምህርት ቤት መሳሪያዎች |
| JGD/JGE | የተማሪ እገዳ/መባረር ሕጎች |
| JGDA | የአካል ጉዳይ ያለው ተማሪ ዲሲፕሊን አሰጣጥ |
| JGDB | የአካል ጉዳይ ያለው ተማሪ ዲሲፕሊን አሰጣጥ ካባድ የአካል ጉዳት በማድረስ |